

# ምስጋና!

(ለብርቱካን ሚደቅሳ)



ላገር ኩራት ቀጣይነት - ለትውልዱ ባላደራ፣

ጊዜ መርጦሽ ለክንውን - ለታሪክ ፊር ዕጹብ ስራ፣

በለጋነት የናት ጫንቃሽ ፣

የአዕላፋት ዕዳ-ክብር - እንደ ታቦት ተሸክመሽ፣

የስቃይ ቀን . . . የጣር ሌሊት . . . በፈረቃ አሳልፈሽ፣

ለነጻነት ደማቅ ብርሃን - ቀንዲል ሻማ ሆነሽ በርተሽ፣

ላገር ብለሽ፣ ለእኛ ብለሽ . . እንዳንከስም እንደዋዛ፣

አንድ ራስሽን አሳልፈሽ - ለሰጠሽው ሕይወት ቤዛ . . . ፤

. . . *ክፉ ይበል ባርኔጣችን . . ፣*
*ጎንበስ እንበል ካንገታችን . . ፣*
*ይታጠፍ ወገባችን . . ፣*
ክብርት ሆይ! ለጸናሽው ለክብራችን!

ጌታቸው አበራ
መስከረም 2003 ዓ/ም
(ኦክቶበር 2010)